
# እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 1-10/2018 የነበረው የአየር ሁኔታ ግምገማ

ባለፉት የዲሴምበር አስር ቀናት የበጋዉ ደረቅ፣ ፀሃያማ እና ነፋሻማ የአየር ሁኔታ በአብዛኛዎቹ የሀገራች አካባቢዎች ላይ አመዝኖባቸዉ ነበር የተስተዋለዉ፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘም የሌሊት እና የማለዳዉ ቅዝቃዜ በተለይም እሰከ አስሩ ቀናት አጋማሽ ድረስ በአንዳንድ የሰሜን፣ የመካከለኛዉ እና የምስራቅ የሀገሪቱ ደጋማ ስፍራዎች ላይ ጨምሮ ተስተዉሏል፡፡ በተጨማሪም የቀኑ ዝቅተኛ ሙቀት በተጠቀሱ አካባቢዎች ላይ አልፎ አልፎ ከ5 ዲግሪ ሴልሽያስ በታች ሆኖ ተመዝግቧል፡፡ ለመጥቀስም በሀረማያ 0.8፣ በባቲ 2.7፣ በደብረ ብርሃን 3.2፣ በወገልጤና 3.2 እና በቢሾፍቱ 3.8 በዲግሪ ሴልሽያስ ይገኙበታል፡፡ ይሁን እንጂ ከአስሩ ቀናት አጋማሽ በኋላ አንጻራዊ የሆነ የደመና ሽፋን መጨመር በአብዛኛዎቹ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ የተስተዋለ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ በደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል፣ በቤኒሻንጉል ጉሙዝ፣ በምዕራብ እና ደቡብ ኦሮሚያ እንዲሁም መካከለኛዉ አማራ በጥቂት ቦታዎቻቸዉ ላይ አነስተኛ መጠን ያለዉ ተመዝግቧል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ቀደም ብሎ በአንዳንድ የሀገሪቱ ደጋማ ስፍራዎች ላይ ይስተዋል የነበረዉ የሌሊት እና የማለዳዉ ቅዝቃዜ አንፃራዊ በሆነ መልኩ ቀንሶ ተስተዉሏል፡፡


ባለፉት አስር ቀናት የዝናብ መጠን ከሀገሪቱ ቦታ ሽፋን አንፃር ሲገመገም በደቡብ ጎንደር፣ በምዕራብ እና ምስራቅ ጎጃም፣ በከማሽ፣ በመተከል፣ በምስራቅ ወለጋ፣ በኢሉባቦር እና በጅማ፣ በጉጂ እና በቦረና፣ በቤንች ማጂ፣ በደቡብ ኦሞ፣ በሰገን ህዝቦች፣ በከፋ እና በሸካ፣ በሲዳማ እና በጌዴኦ፣ በጥቂት የአገዉ፣ አርሲ እና ባሌ፣ ምስራቅ እና ምዕራብ ሀረርጌ ዞኖች ላይ ከ2-108 ሚ.ሜ የሚደርስ ከ1-7 ቀናት ያህል ዝናብ ነበራቸዉ (ካርታ 1 እና 2) ።

ባለፉት አስር ቀናት የዘነበው የዝናብ መጠን ከመደበኛው ጋር ሲነፃፀር በከማሽ፣ በመተከል፣ ምስራቅ ወለጋ፣ በቦረና፣ በኢሉአባቦራ፣ በጅማ፣ በከፋ እና በሸካ፣ በቤንች ማጂ፣ በደቡብ ኦሞ፣ በሰገን ህዝቦች፣ በጥቂት የባሌ እና አርሲ ዞኖች ላይ መደበኛ እና ከመደበኛ በላይ የሆነ ዝናብ ስርጭት የነበራቸዉ ሲሆን፤ የተቀሩት አካባቢዎች ላይ ከመደበኛ በታች የሆነ ዝናብ ተመዝግቧል (ካርታ 3) ።


ካርታ1   ኢ.ኤ.አ ከዲሴምበር 1 እስከ 10/2018 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ



ካርታ2   እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 1 እስከ 10/2018 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸው ቀናት ብዛት



**ካርታ3 እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 1 እስከ 10/2018 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን ከመደበኛው ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር**





**ከመደበኛ በታች** **መደበኛ** **ከመደበኛ በላይ**

## እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 1-10/2018 የነበረው የአየር ሁኔታ በእርሻው ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተጽዕኖ

ባለፉት የዲሴምበር ወር የመጀመሪያዎቹ አስር ቀናት የበጋው ደረቅ፣ ፀሐያማና ነፋሻማ የአየር ሁኔታ በአብዛኛዎቹ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የተስተዋለ ሲሆን፤ ይህም ሁኔታ መኸር አብቃይ በሆኑት በአብዛኛው የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የነበረው ደረቅ የአየር ሁኔታ ለሰብል ስብሰባና ድህረ ሰብል ስብሰባ አመቺ ሁኔታን የፈጠረ ነበር። ከደረቃማውና ከነፋሻማው አየር ሁኔታ ጋር ተያይዞ የሌሊት እና የማለዳዉ ቅዝቃዜ በተለይም እሰከ አስሩ ቀናት አጋማሽ ድረስ በአንዳንድ የሰሜን፣ የመካከለኛዉ እና የምስራቅ የሀገሪቱ ደጋማ ስፍራዎች ላይ ጨምሮ  የታየ ሲሆን ይህም ሁኔታ በአንዳንድ ቋሚ ሰብሎችና በፍራፍሬ ተክሎች እድገት ለይ እንዲሁም በእንስሳት ምርት ላይ አሉታዊ ጎን ነበረው፡፡ በአንጻሩ ከአስሩ ቀናት አጋማሽ በኋላ በአየር ውስጥ የእርጥበት መጨመር ከመኖሩ ጋር ተያይዞ በአብዛኛዎቹ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ የሌሊቱና የማለዳው ቅዝቃዜ ጋብ ያለበት ሁኔታ የተስተዋለ በመሆኑ በደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል፣ በምዕራብ ኦሮሚያ እና ደቡብ ኦሮሚያ እንዲሁም መካከለኛዉ አማራ በጥቂት ቦታዎቻቸዉ ላይ አነስተኛ መጠን ያለዉ እርጥበት የተመዘገበ ሲሆን ይህም የተገኘዉ እርጥበት  እድገታቸውን ላልጨረሱ ሰብሎች፣ ለቋሚ ተክሎች የውኃ ፍላጎት መሟላት በጎ ጎን የነበረው ከመሆኑም ባሻገር ለአርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች ለግጦሽ ሳርና ለመጠጥ ውኃ አቅርቦት በጎ ገጽታ ነበረው (ካርታ 4) ፡፡


ካርታ 4  እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 1-10/2018 የነበረው የእርጥበት መጠን በሚ.ሜ




## እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 1-10/2018 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሀው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተጽዕኖ

እ.ኤ.አ ከዲሰምበር 1-10/2018 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ የነበረው ገፅታ በተመለከተ በአገሪቱ በአብዛኛዎቹ ተፋሰሶች ላይ ደረቅ፣ ፀሃያማ እና ነፋሻማ የአየር ሁኔታ አመዝኖባቸው ተስተዉሏል$ በሌላ በኩል በጥቂት የመካከለኛ ምስራቃዊ□ባሮአኮቦ፤ የመካከለኛው አበይ፤ የታችኛዉ ኦሞጊቤ፤ ስምጥ ሸለቆ፤ ገናልዳዋ አዋሳኝ ተፋሰሶች ላይ መጠነኛ የእርጥበት ሁኔታ የተገኘ ሲሆን በተቀሩት በአብዛኛው የአገሪቱ ዋና ዋና ተፋሰሶች ላይ የበጋው ፀሃያማ፣ ነፋሻማና ደረቅ የአየር ሁኔታ አመዝኖባቸዉ ተስተውላል (ካርታ 5)::

ካርታ 5 እ.ኤ.አ <u>ከዲሴምበር</u> ከ1 እስከ 10/2018 ድረስ በተፋሰሶች የነበረው የእርጥበት ሁኔታ




## <u>እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 11-20/2018 የሚኖረው</u>

# የአየር ሁኔታ አዝማሚያ

በመደበኛ ሁኔታ ከሰሜን ንፍቀ ክበብ ወደ ሀገራችን ከሚገባው ደረቅና ቀዝቃዛ የአየር ጠባይ ምክንያት በብዙ የሀገሪቱ ክፊሎች ላይ የበጋው ደረቅ፣ ፀሐያማና ነፋሻማ የአየር ሁኔታ የሚጎላበት ጊዜ ነው። በመሆኑም በተለያዩ ቦታዎች ላይ የሌሊቱ እና የማለዳው ቅዝቃዜ አንጻራዊ ጥንካሬ ሊያሳይ ይችላል።

በአጠቃላይ በሚቀጥሉት አሥር ቀናት ደረቃማው የአየር ሁኔታ በብዙ የሀገሪቱ ሥፍራዎች ላይ ሰፍኖ እንደሚቆይ እና ከዚሁም ጋር ተያይዞ በተለይም በደጋማ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ የሌሊቱና የማለዳው ቅዝቃዜ ሊጠናከር እንደሚችል የሚጠበቅ ሲሆን፤ በሌላ በኩል በጥቂት የምዕራብና የደቡብ ኦሮሚያ፤የደቡብ በሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል በተጨማሪም በሰሜንና በደቡብ ወሎ ዞኖች ላይ አነስተኛ መጠን ያለው ዝናብ ሊኖር እንደሚችል የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ።

## እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 11-20/2018 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በእርሻው ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተጽዕኖ

በሚቀጥለው የዲሴምበር ወር ሁለተኛው አስር ቀናት በአብዛኛው የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የበጋው ደረቅ፣ ፀሓያማና ነፋሻማ የአየር ሁኔታ አመዝኖባቸው እንደሚቆይና በአንዳንድ ቦታዎች ላይም የሌሊቱና የማለዳው ቅዝቃዜ ቀጣይነት እንደሚኖረው በተሰጠው የአየር ሁኔታ ትንበያ ላይ ተመልክቷል፡፡ በመሆኑም የሚጠበቀው ደረቃማ የአየር ሁኔታ በመከናወን ላይ ለሚገኘው የሰብል ስብሰባን ድህረ ሰብል ስብሰባ እንቅስቃሴ በጎ ጎን እንደሚኖረው ይታመናል፡፡ በሌላ መልኩ ከደረቃማው የአየር ሁኔታ ጋር ተያይዞ በአንዳንድ ደጋማ አካባቢዎች ላይ የሌሊቱና የማለዳው ቅዝቃዜ ሊጠናከር እንደሚችል የተተነተኑ የትንበያ መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡ ይህም ሁኔታ በተለይም በመስኖ በመታገዝ በሚለሙ አትክልቶች፣ የፍራፍሬ ተክሎችና በቋሚ ሰብሎች እንዲሁም በእንስሳት ምርታማነት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ሊኖረው ስለሚችል አስፈላጊውን ዝግጅትና ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ምንም እንኳን አነስተኛ መጠን ያለው እርጥበት ሊኖራቸው እንደሚችል በትንበያው ላይ የተጠቀሱት ጥቂት የምዕራብና

የደቡብ ኦሮሚያ እንዲሁም የደቡብ በሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል የሚጠበቀው እርጥበት ለሚያከናውኑት የእንስሳት ልማትም ሆነ ለሰብሎችና ለቋሚ ተክሎች አዎንታዊ ጎን ቢኖረውም በሌላ በኩል  የዝናብ ወቅታቸው ባልሆነው የሰሜንና የደቡብ ወሎ ዞኖች  የሚጠበቀው አነስተኛ እርጥበት በሰብል ስብሰባና ድህረ ሰብል ስብሰባ ላይ በተወሰኑ ቦታዎች ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ሊኖረው ስለሚችል አርሶ አደሮች በየጣልቃው የሚኖረውን ምቹ ሁኔታ ከግምት በማስገባት የደረሱ ሰብሎችን በአግባቡና በጊዜው እንዲሰበስቡ ይመከራሉ፡፡

## እ.ኤ.አ.ከዲሰምበር 11-20/2018 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በውሃው ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥሉት አስር ቀናትም የበጋው ፀሃያማ፤ ነፋሻማና ደረቅ የአየር ሁኔታ በአብዛኛዎቹ የአገሪቱ ተፋሰሶች ላይ አመዝባቸዉ የሚቆይ ቢሆንም በጥቂት የምዕራብና የደቡብ ኦሮሚያ የአገሪቱ ክፍልሎች ባሉ ተፋሰሶች ላይ አነስተኛ መጠን ያለው ዝናብ ሊኖር እንደሚችል ትንበያው ይጠቁማል፡ ስለሆነም አልፎ አልፎ በጥቂት የላይኛው ዋቢሸበሌ፤ የመካከለኛው አዋሽ አዋሳኝ ከፍተኛ ቦታዎች፤ የላይኛው ኦሞጊቤና የላይኛውና የመካከለኛው ገናሌዳዋ ተፋሰሶች ላይ አነስተኛ መጠን ያለዉ ዝናብ እንደሚያገኙ ይጠበቃል፡ የተቀሩት አብዛኛዎቹ የአገሪቱ ተፋሰሶች ለይ ደረቅ የአየር ሁኔታ አመዝኖባቸዉ ይቆያሉ፡